# ፖሊሲ

የሞንትጎመሪ ካውንቲ የትምህርት ቦርድ

***ተዛማጅ ሠነዶች፦*** BLB-EA ፣ BLC፣ GJC-RA፣ GJD-RB፣ JGA-RB
***ኃላፊነት ያለው ጽ/ቤት፦*** የትምህርት ቦርድ

## የአቤቱታዎች (የይግባኝ) ዳኝነት ቅደም-ተከተል ህጎች

**A.** **ዓላማ**

የተብራራ የሜሪላንድ ኮድ/ህግ፣ የትምህርት አንቀጽ፣ ንዑስ ክፍሎች 4-205፣ላይ በተደነገገው ስልጣን መሰረት የፀደቁትን የአሰራር ሥርአት ለመደንገግ 6-202፣ 6-203፣ እና 7-305፣ይህም ለሞንጎመሪ ካውንቲ የትምህርት ቦርድ (ቦርድ) የሚቀርቡ ሁሉንም ይግባኞች የሚመራ እና በቦርዱ የሚካሄዱ የማህበረሰብ ይግባኝ ዳኝነት በት/ቤቶች ሱፐርኢንተንደንት ለቦርዱ የሚቀርብ ሀሳብ ወይም የት/ቤቶች ሱፐርኢንተንደንት የመጨረሻ ውሳኔን በመጠየቅ በሌሎች ውሳኔዎች እስካልተተኩ ድረስ አሉታዊ ተጽዕኖ ባጋጠማቸው ሰዎች የሚቀርቡ ይግባኞች ናቸው። በተለይ በስቴት የትምህርት ቦርድ ህግ ወይም መተዳደሪያ ደንብ የተደነገገ፣ የሞንጎመሪ ካውንቲ የትምህርት ቦርድ ፖሊሲዎች፣ ወይም የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ደንቦች ላይ በተደነገገው መሠረት እንደ ልዩ ትምህርት እና የተማሪዎች ዝውውር ይግባኞችን የሚመለከቱ ጉዳዮች ይሆናሉ።

**B.** **ሂደት እና ይዘት**

1. ትርጉም

a) ቦርድ ማለት የሞንትጎመሪ ካውንቲ የትምህርት ቦርድ ነው።

b) የጊዜ ስሌት፣ ቀናት በሜሪላንድ ህግ 1-203፡ መሰረት ይሰላሉ

(1) መነሻ ነጥብ – በእነዚህ ደንቦች ወይም በማንኛውም አግባብነት ባለው ህግ የተደነገገውን ማንኛውንም ጊዜ ሲሰላ ከተወሰነው የጊዜ ገደብ በኋላ ያለው ቀን ወይም ክስተቱ የጀመረበት ቀን አይካተትም። እና፣ ድርጊቱ ከተፈጸመበት ቀን ቀጥሎ ያለው ቅዳሜ፣ እሁድ ወይም የበዓል ቀን ከሆነ ይቆጠራል።

(2) የመጨረሻ ነጥብ – በዚህ ደንብ ለተደነገገው ለማንኛውም ጊዜ ወይም በማንኛውም አግባብ ባለው ደንብ የመጨረሻውን ቀን ሲሰላ የቦርዱ ጽሕፈት ቤት በጊዜው በመደበኛ የሥራ ሰዓት ክፍት ካልሆነ በሚቀጥለው የቦርዱ ጽሕፈት ቤት ክፍት በሚሆንበት ቀን ሰነዶቹ ይቀርባሉ።

ጊዜ ማራዘም እና ማሳጠር – በተገቢ ምክንያት ቦርዱ በራሱ ተነሳሽነት ወይም በአንደኛው ወገን ጥያቄ በማንኛውም ጊዜ ማንኛውንም ሰነድ ለማቅረብ ወይም ማንኛውንም ማስታወቂያ ለማድረስ በስቴት ህግ የጊዜ ገደብ የሚገደብ ካልሆነ በስተቀር በእነዚህ ደንቦች ላይ የተደነገገውን ጊዜ ሊያሳጥር ወይም ሊያራዝም ይችላል።

c) በዚህ ደንብ መሠረት ቀርቧል/ፋይል ተደርጓል ወይም እየቀረበ/ፋይል እየተደረገ ካለ ለቦርዱ

ደርሷል ማለት ነው። አቤቱታ/ይግባኝ በተማሪ ወይም በተማሪ ወላጅ ወይም አሳዳጊ አማካይነት ሊቀርብ ይችላል። በተማሪ የቀረበ ይግባኝ ከሆነ፣ የተማሪው(ዋ) ወላጅ ወይም አሳዳጊ የይግባኙ ማሳወቂያ እንዲደርሳቸው ስለሚደረግ በይግባኙ ላይ አስተያየት ለመስጠት እድል ይሰጣቸዋል።

d) አካል ወይም አካላት ማለት እያንዳንዱ ጉዳዩ የሚመለከተው ሰው፣ ቡድን ወይም ጉዳዩ እንደሚመለከተው አካል የተሰየመ ወይም ተቀባይነት ያለው አካል፥ ተማሪን፣ ወላጅን፣ የወላጅ ምትክ ወይም የተማሪን አሳዳጊን እና ሱፐርኢንተንደንትን ያካትታል። ሰብሳቢ ኦፊሰሩ(ሯ) ማንኛውንም ሌላ ሰው፣ ቡድን ወይም አካል ለተወሰኑ አላማዎች እንደፍላጎቱ ባህሪ እና መጠን እንዲሳተፍ መፍቀድ ይችላል።

e) ዳኝነቱን የሚመራ ኦፊሰር ማለት ጉዳዩ በችሎት ከመታየቱ በፊት ምርመራ የሚያካሄድ የችሎት መርማሪ ማለት ነው። የቦርዱ ዳኝነት ሰብሳቢ ኦፊሰር ማለት፡- ፕሬዚዳንቱ ወይም ፕሬዚዳንቱ በማይኖሩበት ጊዜ ምክትል ፕሬዚዳንቱ ወይም ሁለቱም በማይኖሩበት ጊዜ በፕሬዚዳንቱ የተሰየመ(ች)/የተወከለ(ች) ወይም እንደዚህ አይነት ስያሜ ከሌለ በቦርዱ የሚመደብ አካል ማለት ነው።

f) ሱፐርኢንተንደንት ማለት የትምህርት ቤቶች ሱፐርኢንተንደንት ወይም ተወካይ ማለት ነው።

g) የጽሁፍ ማስታወቂያ በዚህ ህግ መሰረት የተሟላ የሚሆነው—

(1) አቅራቢው ወገን በእጅ ከሰጠ ወይም በትክክል ሲያደርስ ነው፣

(2) ሠነዶቹን በዩናይትድ ስቴትስ የፖስታ አገልግሎት በኩል ተመዝግቦ እንዲላክ ወይም በአፋጣኝ መልእክት/ኤክስፕረስ ሜይል አስመዝግቦ መላክ ወይም እንደ Fed Ex፣ UPS ወይም DHL የመሳሰሉ የመልክት አገልግሎት ሰጭ ድርጅቶች አማካይነት መልክቱን ከመነሻው ክትትል ማድረግ እና ማረጋገጥ በሚያስችል ሁኔታ መላክ፣ ሠነዶቹ መቅረብ ያለባቸው ቀን ከማለፉ በፊት፣ MCPS የፖስታ አድራሻ መድረስ አለበት።

(3) የሚመለከታቸው ወገኖች በኢሜል እንዲደርሳቸው ከተጠየቀ ኢሜል የተላከበት ቀን።

2. ተፈፃሚነት

a) ይህ ህግ በቦርዱ የዳኝነት /quasi-judicial ኃላፊነቶች ውስጥ ይግባኞችን የማከናወን መመሪያ ይሆናል። የቦርድን ህግ ለማውጣት ወይም ፖሊሲ የማውጣት ተግባሮችን በሚመለከት ተፈፃሚ አይሆኑም።

b) በእነዚህ ደንቦች ላይ የተካተቱት ሂደቶች ተፈጻሚነት የሚኖራቸው በትምህርት አንቀፅ፣ ክፍል 4-205(c)፣ 7-305፣ 6-202፣ እና 6-203 እንዲሁም በትምህርት አንቀፅ ላይ በተገለፀው የአካባቢው የቦርድ አሰራር ሂደት ነው።

(1) በክፍል 4-205(c) የተመለከቱት አፈጻጸሞች የቦርዱ ህጎች እና መመሪያዎችን ወይም የካውንቲውን የህዝብ ትምህርት ቤቶች አስተዳደር ስርዓት በሚመለከቱ ቅሬታዎች እና አለመግባባቶች ላይ የትምህርት ቤቶች ሱፐርኢንተንደንት በሚወስኑት ይግባኝ ላይ ነው። በሜሪላንድ ህግ መሰረት፣ እንደዚህ አይነት የትምህርት ቤቶች ሱፐርኢንተንደንት ውሳኔዎች በ 30 ቀናት ውስጥ ለቦርዱ ይግባኝ መቅረብ አለባቸው።

(2) በክፍል 6-202(a) ስር ያሉ የማጣራት ዳኝነት የትምህርት ቤቶች ሱፐርኢንተንደንት የምስክር ወረቀት ያላቸውን ሰራተኞች ለማገድ ወይም ለማባረር በሚያቀርቡት ሀሳብ ላይ ያተኮረ ነው። (ክፍል 6-201(b)(iv))።

(3) በአንቀጽ 6-203 ስር የሚካሄዱት ዳኝነቶች በችሎት መርማሪ አማካይነት ለመጀመሪያ ጊዜ ለቦርዱ የቀረቡ ጉዳዮች ናቸው።

(4) በአንቀጽ 7-305(c) ስር ጉዳዩን የይግባኝ ዳኝነቱ የሚመለከተው ተማሪዎችን ከ10 የትምህርት ቀናት በላይ ማገድ ወይም ተማሪዎችን ማባረር የተፈቀደ መሆኑን በትምህርት ቤቶች ሱፐርኢንተንደንት ከተረጋገጠ ነው። በሜሪላንድ ህግ፣ እንደዚህ አይነት እገዳዎች በ10 ቀናት ውስጥ ይግባኝ መቅረብ አለባቸው።

3. ስለ አጣሪ ችሎት ይግባኝ ወይም ጥያቄዎች/አቤቱታዎች-ክፍል 4 - 205 (c)

a) ለቦርዱ የሚቀርቡ ይግባኞች የመጨረሻው እርምጃ ወይም የት/ቤቶች ሱፐርኢንተንደንት ውሳኔ በይግባኝ አቅራቢው(ዎች) ላይ አሉታዊ ተጽእኖ ያሳደሩ መሆን አለባቸው። በዚህ አንቀጽ ዓላማ መሠረት፥ የትምህርት ቤቶች ሱፐርኢንተንደንት በ 45 ቀናት ውስጥ ስለ ይግባኙ እርምጃ ካልወሰደ(ች)፣በይግባኝ አቅራቢው(ዋ) ምርጫ፣ለቦርድ ይግባኝ ማለትን የትምህርት ቤቶች ሱፐርኢንተንደንት ውድቅ እንዳደረገ(ች) ሊቆጠር ይችላል።

b) በክፍል 4-205(c) መሠረት እያንዳንዱ ለቦርድ መቅረብ ያለበት ይግባኝ የት/ቤቶች ሱፐርኢንተንደንት ወይም ተወካይ በወሰደው የመጨረሻ እርምጃ ወይም ውሳኔ ይግባኝ ባይን ይጎዳል ተብሎ የሚታሰብ ከሆነ በ 30 ቀናት ውስጥ በጽሁፍ መግለጫ ለቦርዱ በማቅረብ መጀመር አለበት። እያንዳንዱ ይግባኝ ይግባኙን በሚወስድ አካል መፈረም እና የእያንዳንዱን ስም መጻፍ፣ መደበኛ የደብዳቤ እና የኢሜል አድራሻ እንዲኖርበት ያስፈልጋል።

c) በይግባኝ ጥያቄ ማሳወቂያ ወይም የይግባኝ ጥያቄ ከቀረበበት 10 ቀናት ውስጥ፣ ይግባኙን የጠየቀ(ች)ው ግለሰብ ወይም ሰዎች ቅጂውን ለት/ቤቶች ሱፐርኢንተንደንት በማድረግ እንደሚከተለው ለቦርዱ ማቅረብ አለባቸው።

(1) ቦርዱ ውሳኔ እንዲሰጥበት በይግባኝ የቀረቡትን ጉዳዮች ግልጽና አጭር መግለጫ

(2) ይግባኝ ባይ(ዮች) ይግባኙን ይደግፋል ብለው ያመኑበትን ማስረጃ(ዎች) ግልጽና አጭር መግለጫ

(3) በትምህርት ቤቶች ሱፐርኢንተንደንት ስለተሰጠው ብይን በይግባኝ አቅራቢው(ዋ) በኩል የሚቀርበው የክርክር መግለጫ

(4) በይግባኝ አቅራቢው(ዋ) ጠቃሚ ነው ተብሎ የሚታመን በእጁ(ጇ) የሚገኝ(ኙ) ሰነዶች ቅጂ

d) በክፍል 3c) መሠረት አስፈላጊ መረጃዎችን እና ሰነዶችን ከተረከበ በኋላ የትምህርት ቤቶች ሱፐርኢንተንደንት ተጨማሪ መረጃ ወይም የይግባኝ መደገፊያ ሰነዶችን ማቅረብ እና ቅጂውን ለይግባኝ ሰሚው አካል መስጠት ይችላል።

(1) ከቦርድ ፖሊሲ JEE ጋር ስለተያያዙ ውሳኔዎች ይግባኝ፣ ስለ ተማሪ ዝውውር፣ የትምህርት ቤቶች ሱፐርኢንተንደንት በ10 የትምህርት ቀናት ውስጥ ለቦርዱ ቢሮ ምላሽ መስጠት ይጠበቅበታል።

(2) በክፍል 4-205(c) ስር ለተመለከቱት ሌሎች የይግባኝ ጥያቄዎች የትምህርት ቤቶች ሱፐርኢንተንደንት በ15 ቀናት ውስጥ ለቦርዱ ቢሮ ምላሽ መስጠት ይችላል።

(3) የት/ቤቶች ሱፐር ኢንተንደንት የሚሰጠው ምላሽ የትምህርት ቤቶች ቢሮ ተሳትፎን የሚጠይቅ ከሆነ፣ ከላይ B.3.d(1-2) በተደነገገው መሠረት ት/ቤቶች የተዘጉባቸው ቀናት አይቆጠሩም።

e) የትምህርት ቤቶች ሱፐርኢንተንደንት ካቀረቡ በኋላ በአምስት የስራ ቀናት ውስጥ ይግባኝ አቅራቢው በትምህርት ቤቶች ሱፐርኢንተንደንት ለቀረበው ጭብጥ ምላሽ ተጨማሪ ማስረጃዎችን፣ ሰነዶችን ማቅረብ ይችላል/ትችላለች እና ቅጂውን ለት/ቤቶች ሱፐርኢንተንደንት ይሰጣል።

f) የጊዜው ገደብ በስቴት ህግ ተደንግጎ ካልሆነ በስተቀር የጊዜውን መራዘም ምክንያት በአፋጣኝ ይግባኙ ለሚመለከታቸው ወገኖች የጽሁፍ ማስታወቂያ ከተሰጣቸው ቦርዱ ወይም የቦርዱ ተወካይ በእያንዳንዱ ጉዳይ ላይ ለሁለቱም ወገኖች ምላሽ የሚሰጥበትን የጊዜ ገደብ ለማራዘም ይችላል። አሳማኝ ምክንያቶች የሚያጠቃልሉት፣ ነገር ግን በዚህ ብቻ ያልተገደበ ሲሆን፣ብዛት ያለው ሪኮርድ/መዝገብ፣ በርካታ ሰነዶች፣ ወይም በርካታ ምንጮችን መመርመርና ማገናዘብ አስፈላጊ ከሆነ ነው።

g) በተጨማሪም፣ ቦርዱ ተጨማሪ መረጃ ወይም ሰነድ እንዲቀርብ ከሁለቱም ወገኖች ሊጠይቅ ይችላል።

h) የትኛውም ወገን የቃል ክርክር ወይም ማስረጃ የሚደመጥበት ችሎት እንዲካሄድ ወይም ለይግባኝ ውሳኔ አሰጣጥ ሁለቱም አስፈላጊ መሆኑ ከታመነ፣ በክፍል 3c) ላይ የተገለጸውን ምክንያት አጭር መግለጫ፣ ክፍል 3i) ወይም ክፍል 3j) ወይም ሁለቱንም በዚህ ውስጥ የተገለጹትን ጉዳዮች የሚመለከት ማረጋገጫ ማካተት አለበት።

i) በክፍል 3c) በተጠቀሰው ጊዜ ውስጥ ይግባኝ ካልቀረበ ወይም በክፍል 3d) በተጠቀሰው ጊዜ ውስጥ የሚፈለጉት መግለጫዎች ካልቀረቡ ቦርዱ ወይም የቦርዱ ተወካይ ይግባኙን ውድቅ ለማድረግ ይሄ በቂ ምክንያት ይሆናል።

j) በአንቀጽ 4-205 (c) መሠረት የቀረቡ ይግባኞች የሚገናዘቡት በተከራካሪ ወገኖች በጽሑፍ የተሰጡትን ሰነዶችና ክርክር መሠረት በማድረግ ነዉ። ቦርዱ የሁለቱንም ወገኖች ጥያቄ ሊፈቅድ ወይም –

(1) በቀረቡት ጉዳዮች ላይ የቃል ክርክር እንዲካሄድ ወይም

(2) በዚህ ደንብ ክፍል 5 መሰረት ክርክር የሚሰማበት ችሎት እንዲካሄድ ሊመራ ይችላል። ቦርዱ የቃል ክርክር ወይም የመደበኛ ችሎት ጥያቄ/ምርመራ እንዲካሄድ ለመፍቀድ የሚያገናዝባቸዉነገሮች—

(a) የተካተቱት ጉዳዮች ህገ-መንግስታዊ ወይም ትርጉም ባለዉ መልኩ ለህዝብ አስፈላጊ መሆናቸዉን፣

(b) የተነሱት ጉዳዮች መፍትሄ በትምህርት ስርአቱ አስተዳደር ውስጥ ቀዳሚ እሴት ሊኖረው የሚችል መሆኑን፣

(c) ጉዳዩ አንዳንድ ጉልህ የሆነ የሰራተኛ መብትን የሚመለከት ውሳኔ የሚሻ እና፣ እና ባለው የይግባኝ ሂደት በአጥጋቢ ሁኔታ ሊረጋገጥ የማይችል ከሆነ እና/ወይም

(d) በቦርድ ውሳኔ መሠረት አግባብነት ያላቸው ሌሎች ምክንያቶች ካሉ።

k) ቦርዱ ማስረጃ የሚደመጥበት ችሎት አስፈላጊ መሆኑን በሚወስንበት ጊዜ፣ ጉዳዩን ወደ መርማሪ አካል ለመምራት ካልፈቀደ በስተቀር ቦርዱ ችሎቱን ያካሂዳል። ቦርዱ በመጀመሪያ ደረጃ እንዲህ ያለውን ጉዳይ ወደ ችሎት አጣሪ ይመራ እንደሆነ ለመወሰን ከሚያጤናቸው ጉዳዮች መካከል–

(1) ረዘም ያለ ጊዜ የሚወስድ ማስረጃ የሚደመጥበት ችሎት የሚያስፈልግ በክርክሩ ጭብጥ ውስጥ ያሉ እውነታዎች መኖራቸውን ማጣራት፣ እና/ወይም

(2) ጉዳዩ በችሎት አጣሪ መገምገም ያለባቸው በርካታ ሪኮርዶች፣ ብዙ ሰነዶች፣ወይም ተጨማሪ መረጃዎች ካሉ ለቦርድ ውሳኔ ከመቅረቡ አስቀድሞ እንዲገመገም ማድረግ።

4. የይግባኝ ጥያቄ ወይም የምርመራ ዳኝነት ጥያቄዎች– አንቀጽ 6-202(a) and 7-305(c)

a) አንቀጽ 6-202(a)

(1) በአንቀጽ 6-202(a) ድንጋጌ መሠረት ለቦርዱ አጣሪ ችሎት የሚቀርቡ ጥያቄዎች ከትምህርት ቤቶች ሱፐርኢንተንደንት የሚቀርበው ሀሳብ አስተማሪን፣ ርእሰ መምህርን፣ ተባባሪ ሱፐርኢንተንደንትን ወይም ሌላ ሠርተፊኬት ያለውን ሰራተኛ ከሥራ ለማገድ ወይም ማሰናበትን የሚመለከት ከሆነ ነው።

(2) (ሠርተፊኬት ያለው/ያላት ሰራተኛ ከሥራ እንዲታገድ/እንድትታገድ ወይም እንዲባረር/እንድትባረር የቀረበ ሃሳብን በተመለከተ) በአንቀጽ 6-202(a) መሠረት የሚቀርብ እያንዳንዱ የይግባኝ ችሎት ጥያቄ ግለሰቡ(ቧ) ከታገደ(ች)በት ቀን ጀምሮ ባሉት 10 ቀናት ውስጥ የጽሁፍ ጥያቄ ለቦርዱ መቅረብ አለበት፥ የይግባኙ ግልባጭ እና የትምህርት ቤቶች ሱፐርኢንተንደንት የውሳኔ ሃሳብ እና የስብሰባ ጊዜ (የፅሁፍ ማሳወቂያ ከተሰጠበት 10 ቀናት በላይ) የክርክር ችሎት እንዲካሄድ በጽሑፍ ጥያቄ ከሌለ ቦርዱ በቀረበው አስተያየት/ሪኮመንዴሽን መሠረት ይወስናል።

(a) በአንቀጽ 6-202 (a) ድንጋጌ መሰረት እንዲህ ዓይነቱ ማሳወቂያ ግለሰቡ(ቧ) ለቦርድ የይግባኝ ችሎት ጥያቄ የማቅረብ መብት ወይም፣ በአማራጭ ጉዳዩ በግልግል ዳኝነት እንዲታይ የመጠየቅ መብት እንዳለዉ/እንዳላት ጭምር ያሳዉቃል። ለቦርድ ወይም ለግልግል ዳኛ ቀርቦ እንዲታይ የቀረበው ጥያቄ በማስታወቂያው ውስጥ በተጠቀሰው ጊዜ ውስጥ ካልደረሰ፣ የትኛውንም

ዓይነት የይግባኝ ችሎት የመጠየቅ መብቱ(ቷ) እንዳበቃ ይቆጠራል እና ቦርዱ ከትምህርት ቤቶች ሱፐርኢንተንደንት በቀረበው አስተያየት መሰረት ያጸድቃል። ግለሰቡ/ቧ በግልግል ዳኝነት እንዲታይ በተለይ ካልገለጸ/ች፣ ጥያቄዉ በቦርዱ የይግባኝ ችሎት ጥያቄ እንደቀረበ ተደርጎ ይቆጠራል/ይታሰባል።

(b) ጉዳዩ በግልግል ዳኛ ችሎት እንዲደመጥ ግለሰቡ(ቧ) ከጠየቀ(ች) ቦርዱ ጉዳዩን ወደ ትምህርት ቤቶች ሱፐርኢንተንደንት ይመራዋል፣ አንቀጽ 6-202(a) ላይ በተደነገገው መሰረት የግልግል ዳኛን ለመምረጥ በሂደቱ ውስጥ የሚሳተፉ አግባብ ያላቸውን ሰራተኞች ይሰይማል። በሜሪላንድ ዩኒፎርም የግልግል ህግ በሚመራው የዳኝነት ግምገማ ተገዢ ሆኖ የግልግል ዳኛው የሚሰጠው ውሳኔ የመጨረሻ እና በግለሰብ እና በቦርዱ ላይ የሚጸና ይሆናል።

(c) በቦርዱ ችሎት ማስረጃ እንዲደመጥ ግለሰቡ(ቧ) ከጠየቀ(ች) ቦርዱ በሚያደርገው ችሎት ሊደመጥ ይችላል ካልሆነም ጉዳዩን ወደ ችሎት አጣሪ ሊመራው ይችላል። በየትኛውም ሁኔታ ቢሆን የይግባኝ ችሎቱ የሚካሄደው በዚህ ፖሊሲ አንቀጽ 5 ላይ በተቀመጡት ሂደቶች መሰረት ነው።

(3) ምንም እንኳን መደበኛ ባይሆንም በክፍል 6-202 (a) መሠረት የትምህርት ቤቶች ሱፐርኢንተንደንት በሚያቀርቡት የውሳኔ ሃሳብ ቦርዱ በራሱ ተገቢ ነው ብሎ ያመነውን ማንኛውንም የውሳኔ እርምጃ ሕግ በሚፈቅደው መንገድ የመወሰን መብቱ የተጠበቀ ነው።

(4) በድርድር የተደረገ የሰራተኛ ስምምነት ለቦርዱ ይግባኝ ለማቅረብ የሚከለክል ከሆነ [ለምሳሌ:- ክርክሩ ወይም የይገባኛል ጥያቄው በቦርዱ እና በሞንትጎመሪ ካውንቲ የትምህርት ማህበር (MCEA) መካከል፣ በቦርዱ እና አገልግሎት ሰጪ ሰራተኞች አለም አቀፍ ህብረት (SEIU)፣ Local 500፣ እና በቦርዱ እና በሞንትጎመሪ ካውንቲ የአስተዳዳሪዎች እና ርእሰ መምህራን ማህበር (MCAAP)) መካከል በተደረጉ ስምምነቶች መሰረት፣በሁለቱም ወገኖች ማለትም የሰራተኞችን ስምምነት የሚወክለው አካል እና ቅሬታ አቅራቢው ወገን ክርክሩ ለቦርድ እንዲቀርብ ወይም የይገባኛል ጥያቄውን ለመስማት በቅድሚያ በጽሁፍ ተስማምተው ካልሆነ በስተቀር ቦርዱ እንደዚህ አይነት አለመግባባቶችን ወይም የይገባኛል ጥያቄዎችን አይቀበልም።

b) አንቀጽ 7-305(c)

(1) በአንቀጽ 7-305(c) ስር እያንዳንዱ ይግባኝ (የተማሪ ከ10 የትምህርት ቀናት በላይ መታገድ ወይም መባረር)፣ በትምህርት ቤቶች ሱፐርኢንተንደንት ለተማሪው(ዋ) ወይም ለወላጅ ወይም ለአሳዳጊ በጽሁፍ የተሰጠው ውሳኔ ይግባኝ መጠየቂያ ወይም በችሎት እንዲታይ የሚቀርብ ጥያቄ በ10 ቀናት ውስጥ ለቦርዱ መቅረብ አለበት። ለተማሪ፣ ለወላጅ፣ ወይም ለአሳዳጊ የሚሰጠው የሱፐርኢንተንደንቱ ማስታወቂያ ለቦርዱ ይግባኝ ለማለት እና በአጣሪ ችሎት እንዲታይ የመጠየቅ መብት እንዳላቸዉ መግለጽ አለበት።

(2) በአንቀጽ 7-305(c) ስር ያሉ ሁሉም የክርክር ዳኝነት ጥያቄዎች (የተማሪ ከ10 የትምህርት ቀናት በላይ መታገድ ወይም መባረር) ቦርዱ በራሱ ምርጫ ወይም የቦርዱ ኮሚቴ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ መመልከት እንዳለበት ካልተወሰነ በስተቀር ወደ መርማሪ ችሎት ይላካሉ። በመጀመሪያ ደረጃ እንዲህ አይነቱን ጉዳይ ቦርዱ ይግባኝ ለመስማት ይፈልግ

እንደሆነ ለመወሰን ግምት ውስጥ ከሚያስገባቸው ጉዳዮች መካከል የሚከተሉት ይገኙበታል፦

(a) ክርክሩ ተጨባጭ እውነታ የሌለው ወይም በክርክሩ ጭብጥ ላይ ያሉት እውነታዎች ረዘም ያለ ማስረጃ የሚደመጥበት ችሎት ሳያስፈልግ በቦርዱ ሊታይ የሚችል ጉዳይ መሆን/አለመሆኑ።

(b) ጉዳዩን በፍጥነት የመፍታት አስፈላጊነት ካለ።

(c) ጉዳዩ ለህዝብ ጠቀሜታ ያለው ከሆነ፣ ለትክክለኛ የት/ቤት አስተዳደር አስፈላጊ ከሆነ፣ ወይም ጥንቃቄ የሚያሻው ጉዳይ በመሆኑ ቦርዱ ማስረጃውን መስማት እንዳለበት ድምዳሜ ላይ ከደረሰ።

(3) ወላጅ/ተማሪ/ህጋዊ አሳዳጊ የመዳኘት መብትን ለመተው ሲፈልጉ (አንቀጽ 7-305(c)) ይህ መብት የተማሪው(ዋ)ን ከ10 የትምህርት ቀናት በላይ መታገድ ወይም መባረርን ብቻ የሚመለከት ነው) (1) ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ሂደቶች በመከተል ጉዳዩ በጽሑፍ ሪከርድ እንዲወሰን እንዲደረግ፣ እና/ወይም (2) በቦርዱ ፊት የቃል ክርክር እንዲደረግ መጠየቅ ይችላሉ።

(a) ጉዳዩ በጽሁፍ ሪከርድ እንዲታይ የጠየቀ(ች)ው ግለሰብ ወይም ሰዎች ግልባጭ ለት/ቤቶች ሱፐርኢንተንደንት በማድረግ ለቦርዱ የሚከተለውን ማቅረብ አለባቸው።

(i) በይግባኙ ላይ የቀረቡ ጉዳዮች አጭር መግለጫ

(ii) ይግባኝ ባይ(ዮች) ይግባኙን ይደግፋል ብለው ያመኑባቸውን ማስረጃዎች ግልጽ/አጭር መግለጫ

(iii) በትምህርት ቤቶች ሱፐር ኢንተንደንት ዘንድ በይግባኝ አቅራቢ(ዎች) ክርክር የተደረገባቸው የትኛውም እውነታዎች፣ ካሉ፣ የጽሑፍ መግለጫ

(iv) ጠቃሚ ነው ተብሎ የሚታመን ወይም በዚህ ላይ የተመሰረተ እና በይግባኝ አቅራቢው (ዎች) ይዞታ ያሉ የሁሉም ሰነዶች ቅጂ

(b) ይህ መረጃ እና ሰነድ ከቀረበ በኋላ ባሉት 10 የትምህርት ቀናት ውስጥ፣ የት/ቤቶች ሱፐርኢንተንደንት ተጨማሪ መረጃ ወይም ይግባኝ የተጠየቀበትን ውሳኔ የሚደግፉ ሰነዶችን ማቅረብ እና ግልባጭ ለይግባኝ ሰሚው አካል ማቅረብ ይችላል/ትችላለች።

(c) በት/ቤቶች ሱፐርኢንተንደንት ከቀረበ በኋላ በአምስት የስራ ቀናት ውስጥ፣ ይግባኝ ጠያቂው አካል ከሱፐርኢንተንደንቱ ለቀረበው ምላሽ የሚሆን ተጨማሪ ሰነዶችን/ማስረጃ ማቅረብ እና ቅጂውን ለሱፐር ኢንተንደንቱ መስጠት አለበት።

(d) ስለይግባኙ ውሳኔ ከሁለቱም ወገኖች ይግባኙን በተመለከተ የቃል ክርክር

አስፈላጊ ነው ብለው ካመኑ፣ ይህ አካል የምክንያቶቹን አጭር መግለጫ ማቅረብ አለበት።

(e) በተጨማሪም፣ ቦርዱ ተጨማሪ ኢንፎርሜሽን/መረጃ ወይም ሰነድ እንዲቀርብ ከሁለቱም ወገኖች ሊጠይቅ ይችላል።

(4) በአንቀጽ 7-305(c) መሠረት የተማሪን ከ10 የትምህርት ቀናት በላይ መታገድ ወይም መባረርን የሚመለከቱ ጉዳዮች በሙሉ በስቴት ድንጋጌዎች በተወሰነው የጊዜ ገደብ ውስጥ መደመጥ እና መወሰን አለባቸው።

c) አንቀጽ 4b(1) ላይ በተገለፀው ጊዜ ውስጥ የይግባኝ ጥያቄ ካልቀረበ፣ ቦርዱ ወይም የቦርዱ ተወካይ ይግባኙን ውድቅ ለማድረግ ወይም በችሎት እንዲሰማ ለመጠየቅ በቂ ምክንያት ይሆናል።

5. የዳኝነት ችሎት

a) አፈጻጸም

የዚህ ክፍል ድንጋጌ በሌላ መልኩ ካልተገለጸ በስተቀር የምርመራ ዳኝነቱ ወይም በቦርዱ ወይም ቦርዱ በሰየመው ኮሚቴ አጣሪ ችሎቶች እና የቃል ክርክሮች ተፈጻሚ ይሆናሉ።

b) የችሎት መርማሪ

የችሎቱ መርማሪ በሜሪላንድ የይግባኝ ሰሚ ችሎት ፊት እንዲቀርብ/እንዲሰራ የተፈቀደለት/ላት ጠበቃ መሆን አለበት/ባት።

c) ማሳወቂያ

(1) በአንቀጽ 7-305(c) ላይ ለሚነሱ ጉዳዮች ካልሆነ በስተቀር ዳኝነት ከመሰማቱ ከ 20 ቀናት በፊት ለሚመለከተው አካል ሁሉ በቦርዱ ወይም በቦርዱ ተወካይ የጽሁፍ ማስታወቂያ መሰጠት አለበት።

(2) እንዲሁም ይህ ማስታወቂያ የችሎቱን ቀን፣ ሰዓት እና ቦታ መግለጽ አለበት። ክሶች፣ ጉዳዮች፣ ወይም እውነታዎችን በተመለከተ ማንኛውም አለመስማማት የይግባኙ አካል ሆኖ ይወሰናል።

(3) እያንዳንዱ ተከራካሪ ወገን ከችሎቱ ቢያንስ አምስት የስራ ቀናት በፊት በችሎት ቀርበው የሚመሰክሩ ምስክሮችን ዝርዝር እና ሁሉንም የሰነድ ማስረጃ ቅጂ ማቅረብ አለበት።

d) ይፋ እና ዝግ ችሎቶች

(1) በአንቀጽ 6-202(a) መሰረት የሚካሄዱ ዳኝነቶች ጉዳዩ በአጣሪ ችሎት እንዲታይ የሚፈልገው አካል እና የት/ቤቶች ሱፐርኢንተንደንት ሁለቱም ወገን ችሎቱ ይፋ እንዲካሄድ በቅድሚያ በጽሁፍ ወይም በሪከርድ ስምምነታቸውን ካላረጋገጡ በስተቀር

በይፋ አይካሄድም።

(2) ይግባኝ ባይ ወይም በችሎት እንዲታይ ፈላጊው አካል በይፋ ችሎት እንዲሆን ካልተጠየቀ በስተቀር በአንቀጽ 7-305 (c) መሠረት የሚታዩ ዳኝነቶች በይፋ አይካሄዱም።

(3) በጠየቀው አካል በቂ ምክንያት ካልቀረበ፣ ቦርዱ በራሱ ውሳኔ ለህዝብ ይፋ እንዲሆን ካልተስማማ፣ ወይም ለህዝብ ይፋ በሆነ ችሎት ዳኝነት እንዲታይ በህግ ካልተፈለገ በስተቀር ሁሉም ችሎት ለህዝብ ይፋ አይደረግም።

e) ውክልና

በእነዚህ ድንጋጌዎች መሠረት ችሎት የሚቀርቡ ወገኖች በሙሉ በሜሪላንድ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ለመከራከር ፈቃድ ካለው/ካላት ጠበቃ ጋር በአካል የመቅረብ መብት አላቸው።

f) መዝገቦች – ትራንስክሪፕት

(1) ሂደቱን የሚመራዉ ኦፊሰር ሁሉንም አቤቱታዎች፣ ምስክሮች፣ ማስረጃዎች/ኤግዚቢቶች እና ሌሎች በሂደቱ ላይ የተካተቱትን ማስታወሻዎች ወይም ቁሳቁሶች የሚያካትት ኦፊሴላዊ መዝገቦችን ያዘጋጃል ወይም እንዲዘጋጅ ያደርጋል/ታደርጋለች።

(2) ይግባኝ የሚጠየቅ ከሆነ መዝገቡ መቅረብ እንዲችል የሁሉም ችሎቶች፣ ክርክሮች ወይም አወዛጋቢ ነገሮች ትክክለኛ መዝገብ በትምህርት ቤቶች ሱፐርኢንተንደንት ዘንድ መቀመጥ አለባቸው።

(3) በሁሉም ተዋዋይ ወገኖች ፍላጎት ከሌለ በስተቀር የማስረጃ አቀራረብን የሚመለከተው የክርክሩ ክፍል በምሕፃረ ቃል ወይም በምልክት መተየቢያ መሣሪያ (ስተኖግራፊክ) ሪከርድ በቦርዱ ወጪ ይከናወናል። ይሁን እንጂ እንደ ሁኔታው በተከራካሪ ወገኖች፣ የአከባቢ የትምህርት ቤቶች ሱፐርኢንተንደንት፣ የአካባቢው ቦርድ፣ ወይም በስቴት ሱፐርኢንተንደንት ካልተጠየቀ በስተቀር ሪከርዱን መገለበጥ አያስፈልግም። የማንኛውም ሂደቶች የተወሰነ ክፍል፣ ወይም በታይፕ የተጻፈ ግልባጭ/ጸሑፍ/ትርንስክሪፕት፣ወጪ በጠያቂዉ አካል የሚሸፈን ይሆናል።

g) የሰብሳቢው ኦፊሰር ተግባርና ስልጣን

የችሎት ሂደቱ ኦፊሰር፣ የምስክሮችን ምርመራ ለመፍቀድ፣ ማስረጃ ለመቀበል፣ በማስረጃ ተቀባይነት ላይ የመወሰን፣ እና ችሎቱን ለሌላ ጊዜ ለማስተላለፍ ወይም ችሎቱን ከጊዜ ወደ ጊዜ ለመበተን/ለማቋረጥ በችሎቱ ላይ ስልጣን አለው/አላት። የችሎት ሂደቱ ኦፊሰር በችሎት ቀርበው የሚመሰክሩ ምስክሮች ሁሉም ቃለ መሐላ እንድፈጽሙ ያስደርጋል። የትምህርት ቤቶች ሱፐርኢንተንደንት ለምስክሮች ቃለ መሃላ እንዲፈጽሙ ማድረግ ይችላል (ክፍል 4-205(b))።

h) ምልአተ ጉባኤ

በአንቀጽ 7-305(c) ስር በቦርዱ ዳኝነት እንዲታይ የሚቀርበው እያንዳንዱ የይግባኝ ጥያቄ መታየት ያለበት በቦርዱ ምልአተ ጉባኤ፣ ወይም ቦርዱ በወከለው ኮሚቴ ምልአተ ጉባኤ ነው።

i) የቅደም ተከተል አሰራር ህግ

ከዚህ እንደሚከተለዉ ካልሆነ በስተቀር፣ ባለጉዳዮች ጉዳያቸውን የሚያቀርቡበት ቅደም ተከተል በሰባሳቢ አፊሰሩ ይወሰናል፡-

(1) የተማሪ መታገድ ወይም መባረር ወይም የፕሮፌሽናል ሰራተኛ መታገድ ወይም መባረርን በሚመለከት ችሎት የት/ቤቶች ሱፐርኢንተንደንት በመጀመሪያ እርምጃ የመውሰድ እና የማስፈጸም ኃላፊነት አለበ(ባ)ት።

(2) በሌሎች ሁሉም ይግባኞች፣ ይግባኝ ባይ በመጀመሪያ ጉዳዩን ያቀርባል/ታቀርባለች።

j) የምሥክሮች ምርመራና የማስረጃ አቀራረብ

(1) ጥብቅ የማስረጃዎች አቀራረብ ውሳኔ በዚህ መሠረት ለሚከናወኑ ግልፅ የዳኝነት ችሎቶች ተፈጻሚነት አይኖራቸውም፣ በእያንዳንዱ ጉዳይ ላይ ተቀባይነት ያለው ግምገማ ማስረጃው አሳማኝ በሆነ መልኩ አግባብነት ያለዉ መሆኑን እና ከእንዲህ ዓይነቱ ተጨባጭ ጉዳይ ጋር በተያያዘ ጉልህ ዋጋ ያለው መሆን አለመሆኑን ያሳያል። ሰብሳቢ አፊሰር የተጠቃለለ ወይም ተደጋጋሚ ማስረጃን መገደብ ወይም ውድቅ ማድረግ እና ተደጋጋሚ መጠይቆችን ማገድ/ማስቆም ይችላል/ትችላለች። የችሎቱ አፊሰር ተሟጋች አካላትን (በማስገደድ ሳይሆን)፣ሲቻል፣ በምክንያታዊነት አለመግባባቶች በማይታዩባቸዉ ጉዳዮች ላይ መስማማት እና በጥቅል መረጃ ከመከራከር ይልቅ ስምምነት እንዲያደርጉ ያበረታታል/ታበረታታለች። ሁሉም የምስክርነት ቃል በቃለመሐላ ይሰጣል።

(2) ማንኛዉም ወገን፣ወይም በጠበቃ ወይም በሌላ ተወካይ የተወከለ/ች አካል፣ጠበቃው ወይም ሌላ ተወካዩ ማስረጃ ማቅረብ፣ ምስክሮችን መጠየቅ/መመርመር እና ለምስክሮች መስቀለኛ ጥያቄ ማቅረብ፣ ተቃውሞ ማቅረብ፣ አስተያየቶችን እና አቤቱታዎችን ሊያቀርቡ ይችላሉ።

(3) የትምህርት ቤቶች ሱፐርኢንተንደንት በአካል ወይም በካውንስል ወይም በተወካይ አማካይነት መቅረብ ይችላል፣ እንዲሁም እንደ ተከራካሪ ወገን ማስረጃ የማቅረብ፣ ምስክሮችን ጥያቄ የመጠየቅ እና መስቀልኛ ጥያቄዎችን የመጠየቅ፣ተቃውሞ የማቅረብ፣ እና ልዩ ሁኔታዎችን እና የመከራከሪያ ሃሳብን የማቅረብ መብት ይኖረዋል/ይኖራታል።

(4) ችሎቱን የሚመራው አፊሰር ሁሉንም ምስክሮች በመስቀልኛ ጥያቄ ሊመረምር ይችላል። ምስክርነቱ/ቷ አግባብነት የሚኖረው ከሆነ የሚመራው አፊሰር ማንኛውንም ሰው በምስክርነት ሊጠራ ይችላል። ቦርዱ በሚያካሄዳቸው ችሎቶች ላይ፣ ማንኛውም የቦርድ አባል ማንኛውንም ምስክር በጥያቄ መመርመር ይችላል።

k) አጭር የጽሑፍ ውል

እያንዳንዱ ተከራካሪ ወገን እና የት/ቤቶች ሱፐርኢንተንደንት በችሎቱ ላይ የሚቀርቡትን እውነታዎች እና የህግ ጉዳዮችን በሚመለከት ሰብሳቢ አፊሰሩ በሚያዘው መሠረት አጭር የጽሁፍ መግለጫ ማቅረብ ይችላሉ። እንዲህ ዓይነቱን የጽሑፍ መግለጫ ጉዳዩ ከመሰማቱ/ከመታየቱ በፊት በማንኛውም ጊዜ ማስገባት ይቻላል። በሰብሳቢ አፊሰር ሲፈቀድ እና በሚወሰነዉ መርሃግብር መሠረት፣ ችሎቱ ከተሰማ በኋላ የጽሑፍ መግለጫ ማቅረብ ይቻላል።

l) የቦርድ ካውንስል

በማንኛውም ችሎት ላይ የቦርዱ ጠበቃ አማካሪ ሆኖ እንዲሳተፍ ሰብሳቢ ኦፊሰሩ ሊጠይቅ ይችላል/ትችላለች።

m) የችሎት አጣሪ ግኝቶች

በመጀመሪያ በችሎት አጣሪው(ዋ) የተሰሙ ጉዳዮች ሁሉ፣ የችሎት መርማሪዉ/ዋ ተጨባጭ ግኝቶችን፣ የሕግ ድንጋጌዎችን መግለጫ፣ እና የውሳኔ ሃሳቦችን ያቀርባል/ታቀርባለች። የይግባኝ ሰሚ መርማሪ የችሎቱን ትራንስክሪፕት፣ኤግዚቢቶች፣ ተጨባጭ ግኝቶች፣ የሚመለከተውን የሕግ ድንጋጌ መግለጫዎች፣ እና ምክረሀሳቦችን ለቦርዱ ያቀርባል/ታቀርባለች። ችሎቱ ከተጠናቀቀ ከ15 ቀናት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ የችሎት መርማሪው(ዋ) የእውነታውን ግኝቶች፣ ህጋዊ ድምዳሜዎችን፣ እና የውሳኔ ሃሳቦችን ለሁሉም ወገኖች እና ለቦርዱ ማስተላለፍ ወይም በፖስታ መላክ አለበ(ባ)ት። በአንቀጽ 7-305 (c) ስር ከሚነሱ ጉዳዮች በስተቀር፣ የችሎት ምርመራና የቃል ክርክር ወይም ከችሎቱ በኋላ የጽሑፍ መግለጫ ለማቅረብ ከተፈቀደ፣ እንደዚህ ዓይነት የቃል ክርክር ወይም የጽሑፍ ማቅረብ ሳይፈጸም፣ ቀዳሚው የሚሆነዉ የቱም ቢሆን፣ የ15 ቀናት የጊዜ ገደብ አይጀምርም።

n) የቃል ክርክር

(1) በችሎት መርማሪ ምክረሀሳብ መሰረት በችሎት መርማሪ ፊት ተሳታፊ የሂደቱ አካላት የቃል ክርክር ሊያቀርቡ ይችላሉ፣ ሆኖም በበቂ በምክንያት ቦርዱ በራሱ ውሳኔ የበለጠ ተጨማሪ ማስረጃ ለመስማት ካልተስማማ በስተቀር ተጨማሪ አዲስ ማስረጃ መቅረብ የለበትም።

(2) በክርክር ዉስጥ ምንም እዉነታ በሌለበት ሁኔታ ይግባኝ የጠየቀው አካል በቦርዱ ፊት የቃል ክርክር ሊያደርጉ ይችላሉ።

(3) በችሎት መርማሪ ፊት እና በግልፅ ችሎት በቦርዱ ፊት ማስረጃ የሚያቀርቡ የሂደቱ አካላት በችሎት መርማሪ ወይም በቦርዱ ፊት የቃል ክርክር ሊያደርጉ ይችላሉ። ግልፅ ችሎት በሚካሄድበት ወቅት ወይም በኋላ፣የጽሑፍ መግለጫ ከቀረበ በኋላ፣ወይም የጽሑፍ ትራንስክሪፕት ሲገኝና ኦፊሰሩ በአንድ በተለየ ጉዳይ ላይ ተገቢነቱን ከተገነዘበ፣ የቃል ክርክር መፍቀድ ይችላል/ትችላለች።

(4) ኦፊሰሩ ለእያንዳንዱ ወገን ለቃል ክርክር የሚፈቀደዉን ጊዜ አስቀድሞ ሊገድብ ይችላል/ትችላለች። ኦፊሰሩ በምክንያት ተጨማሪ ጊዜ ካልፈቀደ/ች በስተቀር፣ በእያንዳንዱ አካል በቦርዱ ፊት የሚቀርብ የቃል ክርክር ከ 30 ደቂቃዎች መብለጥ የለበትም።

(5) በቦርዱ የቃል ክርክር ሲሰማ ለቦርዱ ጠበቃ ማስታወቅ እና እንዲገኝ/እንድትገኝ መጠየቅ ይገባል።

o) ውሳኔ እና ቅደም ተከተል

ችሎቱ ውሳኔውን ወዲያውኑ በቃል ከሚያሳውቀው በተጨማሪ እያንዳንዱ የቦርዱ ውሳኔ እና ትዕዛዝ በጽሁፍ ለሁሉም ወገኖች እንዲደርሳቸው ቅጂዎች ይሰጣሉ። እያንዳንዱ የጽሑፍ ውሳኔ እና ትእዛዝ የጽሑፍ ተጨባጭ ማረጋገጫዎች፣ የሚመለከተው የሕግ አንቀጽ ድንጋጌዎች፣ እና የጉዳዩ ሁኔታ ልዩ መግለጫን የያዙ ይሆናሉ። ችሎቱን ተከትሎ የቦርዱ የመጨረሻ እርምጃ በቦርዱ ስብሰባ ላይ በይፋ ይወሰናል።

p) Ex Parte Communications/የቀድሞ ግንኙነቶች

ጉዳዩ ለቦርድ ይግባኝ በሚቀርብበት ጊዜ ወይም በችሎት መርማሪው እየተፈተሸ ሳለ፣ የሚከተሉት የአሰራር ደንቦች መከናወን አለባቸው፦

(1) የችሎት መርማሪው(ዋ) ሌሎች አካላት በሌሉበት ከማናቸውም ወገኖች ጋር መገናኘት፣ ወይም መነጋገር የለበ(ባ)ትም፣ ወይም ለሌሎቹ ተከራካሪ ወገኖች ቅጅ ሳይሰጥ ወይም አግባብነት ካለው መልስ የመስጠት እድል ሳይሰጣቸው ከአንደኛው ወገን ጋር በጽሑፍ መገናኘት የለበ(ባ)ትም።

(2) ከኦፊሴላዊው የይግባኝ ሂደት ውጭ የቦርድ አባል (a) ከማንኛውም አካል ጋር ይግባኝ በተባሉ ጉዳዮች ላይ መወያየት፣ ወይም (b) የይግባኝ ጉዳዮችን በተመለከተ ከማንኛውም አካል ማንኛውንም የቃል ወይም የጽሁፍ ግንኙነት መቀበል ወይም መከለስ አይችልም።

(3) ጉዳዩ ይፋዊ/ህዝባዊ ሪከርድ ካልሆነ በስተቀር ወይም ለአንዱ አካል ከተሰጠ እና ለሌሎች ሁሉም ወገኖች ወዲያዉኑ ቅጂዎች ተሰጥተው ካልሆነ በስተቀር፣ በይደር/በቀጠሮ ላይ ያለ ጉዳይን በተመለከተ በቦርዱ፣ በቦርድ አባል፣ በችሎት መርማሪ፣ ወይም በ MCPS የአስተዳደር አባል ምንም መረጃ ሊወጣና ሊሰጥ አይችልም።

q) ዳግመኛ ችሎት

(1) በአንድ ጉዳይ ላይ በተሰጠው ውሳኔ እና ትእዛዝ ቅር የተሰኘ አካል ውሳኔው እና ትዕዛዙ ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ ባሉት 30 ቀናት ውስጥ ጉዳዩ እንደገና እንዲታይ ማመልከት ይችላል። ለዳግመኛ ችሎት የሚቀርበው ማመልከቻ ምክንያቶቹን በዝርዝር መግለጽ አለበት፣ እና በቀረበው ማመልከቻ ላይ የሚወሰድ ማንኛውንም እርምጃ የመወሰን ስልጣን የቦርዱ ብቻ ይሆናል።

(2) የተለየ ትእዛዝ ካልተሰጠ በስተቀር፣ዳግም ችሎትም ሆነ ለዳግም ችሎት ማመልከቻ ትዕዛዙን ተፈጻሚ ከማድረግ ወይም በውሳኔው የተጎዱት ሰዎች ውሳኔውን እንዳያከብሩ ይቅርታ አያሰጥም።

(3) ቦርዱ ጉዳዩን እንደገና በሚመለከትበት ወቅት በፊተኛው ችሎት ያልቀረቡትን እውነታዎች፣ የቀደመው ችሎት ከተሰማበት ቀን በኋላ የሚነሱትን እውነታዎች ጭምር፣ አዲስ ትእዛዝ፣ ህግ ወይም ውልን በይፋ መሻር፣ መለወጥ፣ ወይም ቅደም ተከተል ማሻሻል ሊሆን ይችላል።

r) በሌሎች የአሠራር ቅደምተከተል መመሪያዎች ላይ ያለው ውጤት

እነዚህ የአሠራር ሕጎች ቦርዱ በሚያደርጋቸው የዳኝነት ችሎት፣ በችሎት መርማሪ፣ እና ለቦርዱ ይግባኝ በቀረቡ ጉዳዮች፣ ወይም በትምህርት ቤቶች ሱፐርኢንተንደንት ጥያቄ በቦርዱ እንዲታዩ የቀረቡትን ሌሎች ሂደቶች ሁሉ ይተካሉ።

**C. ክለሳ እና ሪፖርት**

ይህ ደንብ በቦርድ የማሻሻያ መርኀ መሰረት ይከለሳል።

***ተዛማጅ ምንጮች፡-*** Md.Code Ann., Education Sections 4-205, 6-202, 6-203, and 7-305; Maryland Rules, Rule 1-203.

***የፖሊሲው ታሪክ፡-*** የፀደቀበት ውሳኔ ቁጥር 227-84፣ኤፕሪል 10, 1984፣ በውሳኔ ቁጥር 536-84፣ አክቶበር 9, 1984፣ በውሣኔ ቁጥር እንደገና ተስተካክሏል። 333-86፣ ጁን 12, 1986፣ እና በውሳኔ ቁጥር 458-86፣ አገስት 12, 1986፣ በውሳኔ ቁጥር 550-88 ሥራ ላይ ውሏል፣ አክቶበር 24, 1988፣ በውሳኔ ቁጥር 1050-91 ተሻሽሏል፣ ዲሰምበር 10, 1991፣ በውሳኔ ቁጥር 18-13 ተሻሻለ። ጃኑወሪ 8፣ 2013 በውሳኔ ቁ. 315-14 ተሻሽሏል፣ ጁን 30/2014 በውሳኔ ቁጥር 415-18 ቴክኒካዊ ማሻሻያ ተደርጓል፣ ሴፕቴምበር 11, 2018 በውሳኔ ቁጥር. 447-23 ተሻሽሏል፣ አክቶበር 26, 2023.ተሻሽሏል።

# የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) የፀረ-መድሎአዊነት መግለጫ

የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) በዘር ሐረግ፣ በጎሣ፣ በቀለም፣ በትውልድ ሐረግ፣ በዜግነት፣ በሃይማኖት፣ በስደት ሁኔታ፣ በጾታ፣ በጾታ መግለጫ፣ በጾታ ማንነት፣በጾታዊ ዝንባሌ፣በቤተሰብ መዋቅር/የወላጅነት ሁኔታ፣ በትዳር ሁኔታ ላይ የተመሰረተ ሕገወጥ አድልዎ ማድረግን ይከለክላል። ዕድሜ፣ ችሎታ (ግንዛቤ፣ ማህበራዊ/ስሜታዊ እና አካላዊ)፣ ድህነት እና ማህበራዊ-ኢኮኖሚያዊ ደረጃ፣ ቋንቋ፣ ወይም ሌላ በህግ ወይም ህገ-መንግሥታዊ ጥበቃ የተደረገላቸው ባህሪያት ላይ የሚደረግ ማናቸውንም ሕገወጥ አድልዎ ይከለክላል። መድሎ ወይም አድሎአዊነት፣ ሕብረተሰባችን ለረዥም ጊዜ እኩልነት፣ ፍትኃዊነት፣ አብሮነት፣ ሁሉን አቀፍነትን፣ ለማስፈን እና ለማዳበር/ለመንከባከብ ሲካሄድ የቆየውን ጥረት ይሸረሽራል/ያበላሻል። ቦርዱ ጥላቻን የሚያራምድ ቋንቋን እና/ወይም ምስሎችን እንዲሁም ምልክቶችን መጠቀምን ይከለክላል፥ በተለይም በትምህርት ቤት ወይም በዲስትሪክት ሥራ ወይም እንቅስቃሴ ላይ ከፍተኛ ማደናቀፍ ሊያስከትል የሚችል ድርጊት-እንቅስቃሴ የተከለከለ ነው። የበለጠ መረጃ ለማግኘት፣ እባክዎ የሞንትጎመሪ ካውንቲ "የትምህርት ቦርድ ፖሊሲ ACA" ይመልከቱ፡- "ከአድሎአዊነት ነጻ የሆነ ፍትሃዊነት፥ ሚዛናዊነት፥ እና የዳበረ ባህል"። ይህ መመርያ እያንዳንዱ ተማሪ ትኩረት የሚሻ መሆኑ(ኗ)ን  እና በተለይም የትምህርት ውጤቶች በምንም አይነት በግለሰብ ትክክለኛ ወይም ይሆናል ተብሎ በሚገመት ግላዊ ባህርያት የሚተነበይ እንደማይሆን የቦርዱን እምነት ያረጋግጣል። ፖሊሲው በተጨማሪም ፍትህ/እኩልነትን/ሚዛናዊነትን የሚያዛቡ ነገሮችን ለይቶ በማወቅ በቅድሚያ መወሰድ ያለባቸው እርምጃዎችን፥ የተዛባ ስውር አመለካከትን፣ ጭፍን/መሠረተ-ቢስ ልዩነት ማድረግን፣ በተቋማት የሚፈጸሙ መዋቅራዊ መሰናክሎችን፣ በትምህርት እና በሥራ ላይ እኩልነት እንዳይኖር ተፅእኖ የሚያደርጉ አሠራሮችን የሚገታ/የሚፃረር መሆኑን ያስገነዝባል። MCPS ለወንድ/ለሴት ልጆች በስካውትነት እና በሌሎች የወጣት ቡድኖች ለመመደብ እኩል ተደራሽነት ይሰጣል።

A. በሜሪላንድ ስቴት ፖሊሲ መሠረት ሁሉም የህዝብ እና በህዝብ የገንዘብ ድጋፍ የሚደረግላቸው ትምህርት ቤቶች እና የትምህርት ቤት ፕሮግራሞች የሚከተሉትን ድንጋጌዎች በማክበር መንቀሳቀስ አለባቸው፡-
   (1) 1964 የፌደራል ሲቪል መብቶች ህግ አንቀጽ VI፣ እና
   (2) በሜሪላንድ ኮድ የትምህርት ደንብ አንቀጽ 26 ንዑስ አንቀጽ 7፣ ይኸውም የህዝብ እና በህዝብ የገንዘብ ድጋፍ የሚደረግላቸው ትምህርት ቤቶች እና ፕሮግራሞች፡-
      (a) በዘር፣ በጎሳ፣ በቀለም፣ በሃይማኖት፣ በጾታ፣ በእድሜ፣ በብሔር፣ በጋብቻ ሁኔታ፣ በፆታዊ ሁኔታ፣ ዝንባሌ፣ የፆታ ማንነት፣ ወይም የአካል ጉዳተኝነት ምክንያት፣ አሁን ባሉት ተማሪዎች ላይ፣ የወደፊት ተማሪዎች ላይ፣ ወይም የአሁን ወይም የወደፊት ተማሪዎች ወላጆች ወይም አሳዳጊዎች ላይ አድልዎ ማድረግ የተከለከለ ነው፣
      (b) በአንድ ግለሰብ ዘር፣ ጎሳ፣ ቀለም፣ ምክንያት የወደፊት ተማሪዎችን መመዝገብ እምቢ ማለት፣ የአሁኑን ተማሪዎች ማባረር፣ ወይም ከአሁን ተማሪዎች፣ የወደፊት ተማሪዎች ወይም የአሁኑ ወይም የወደፊት ተማሪዎች ወላጆችን ወይም አሳዳጊዎችን የሃይማኖት፣ የጾታ፣ የዕድሜ፣ የብሔር፣ የጋብቻ ሁኔታ፣ የፆታ ዝንባሌ፣ የፆታ ማንነት ወይም የአካል ጉዳት፣ የመሳሰሉትን ምክንያት በማድረግ መብቶችን መከልከል፣ ወይም
      (c) የትምህርት ውጤቱ(ቷ) ምንም ይሁን ምን መርሃ ግብሩ ወይም ትምህርት ቤቱ በተማሪው(ዋ) ላይ አድሎአዊነትን ፈጽመዋል የሚል ቅሬታ ባቀረበ(ች) ተማሪ ወይም ወላጅ ወይም አሳዳጊ ላይ ቅጣት ማድረግ፣ ወይም ማንኛውንም ሌላ የበቀል እርምጃ መውሰድ የተከለከለ ነው**

እባክዎን የግንኙነት መረጃ እና የፌዴራል፣ የስቴት፣ ወይም የአካባቢ መረጃ ይዘትን በተመለከተ መስፈርቶቹ በዚህ ሰነድ እትም ላይ ተለውጠው ሊሆን ይችላል፥እና በወቅታዊ መረጃ እንደተተካ ልብ ይበሉ። በዚህ ውስጥ የተካተቱትን መግለጫዎች እና ማመሳከሪያዎችን ወቅታዊ መረጃ ለማግኘት እባክዎን ይህንን በይነመረብ ይመልከቱ፡- www.montgomeryschoolsmd.org/info/nondiscrimination

| በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ተማሪዎች ላይ አድልዎ ሲፈጸም ጥያቄ ወይም ቅሬታ ለማቅረብ አድራሻው ከዚህ በታች የሚገኘው ነው፡-*** | በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ሰራተኞች ላይ ስለሚደርስ መድልዎ ጥያቄ ወይም ቅሬታ ለማቅረብ አድራሻው ከዚህ በታች የሚገኘው ነው፡-*** |
|---|---|
| Director of Student Welfare and Compliance<br>Office of District Operations<br>Student Welfare and Compliance<br>15 West Gude Drive, Suite 200, Rockville, MD 20850<br>240-740-3215 \| SWC@mcpsmd.org | Human Resource Compliance Officer<br>Office of Human Resources and Development<br>Department of Compliance and Investigations<br>45 West Gude Drive, Suite 2500, Rockville, MD 20850<br>240-740-2888 \| DCI@mcpsmd.org |
| 1973 የተሃድሶ ድእንብ ሰክሽን 504 መሠረት ለተማሪ የመገልገያ/አኮሞዴሽን/ጥያቄ ማቅረቢያ አድራሻ ከዚህ በታች የሚገኘው ነው፡- | በአካል ጉዳተኛ አሜሪካውያን ህግ መሠረት ለሰራተኞች የመገልገያ/የአኮሞዴሽን/ጥያቄ ማቅረቢያ አድራሻ ከዚህ በታች የሚገኘው ነው፡- |
| Section 504 Coordinator<br>Office of School Support and Improvement<br>Well-Being and Student Services<br>850 Hungerford Drive, Room 257, Rockville, MD 20850<br>240-740-3109 \| 504@mcpsmd.org | ADA Compliance Coordinator<br>Office of Human Resources and Development<br>Department of Compliance and Investigations<br>45 West Gude Drive, Suite 2500, Rockville, MD 20850<br>240-740-2888 \| DCI@mcpsmd.org |

| ታይትል IX ስር ስለ ፆታዊ መድልዎ፣ ጾታዊ ትንኮሳን ጨምሮ፣ በተማሪዎች ላይ ወይም በሰራተኞች ላይ ስለሚደረግ ጥቃት ጥያቄ ወይም ቅሬታ ለማቅረብ አድራሻው ከዚህ በታች የሚገኘው ነው፡-*** |
|---|
| Title IX Coordinator<br>Office of District Operations<br>Student Welfare and Compliance<br>15 West Gude Drive, Suite 200, Rockville, MD 20850<br>240-740-3215 \| TitleIX@mcpsmd.org |

*ይህ መግለጫ ከተሻሻለው የፌዴራል የአንደኛ ደረጃ እና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ህግ ጋር የተጣለጠ ነው።
**ይህ መግለጫ የሜሪላንድ ዝርዝር ደንብ/ኮድ አንቀጽ 13A.01.07. ጋር የተጣለጠ ነው።
***የመድሎአዊነት ቅሬታዎችን ለሚከተሉት ሌሎች ኤጀንሲዎችም ማቅረብ ይቻላል፡-
U.S. Equal Employment Opportunity Commission (EEOC), Baltimore Field Office, GH Fallon Federal Building, 31 Hopkins Plaza, Suite 1432, Baltimore, MD 21201, 1-800-669-4000, 1-800-669-6820 (TTY); Maryland Commission on Civil Rights (MCCR), William Donald Schaefer Tower, 6 Saint Paul Street, Suite 900, Baltimore, MD 21202, 410-767-8600, 1-800-637-6247, mccr@maryland.gov; Agency Equity Officer, Office of Equity Assurance and Compliance, Office of the Deputy State Superintendent of Operations, Maryland State Department of Education, 200 West Baltimore Street, Baltimore, MD 21201-2595, oeac.msde@maryland.gov; or U.S. Department of Education, Office for Civil Rights (OCR), The Wanamaker Building, 100 Penn Square East, Suite 515, Philadelphia, PA 19107, 1-800-421-3481, 1-800-877-8339 (TDD), OCR@ed.gov, ወይም www2.ed.gov/about/offices/list/ocr/complaintintro.html.

ይህንን ሠነድ ከእንግሊዝኛ ቋንቋ በተጨማሪ በአማራጭ ቋንቋ/ፎርማት ማግኘት ካስፈለገ "Americans with Disabilities Act" ድንጋጌ መሠረት MCPS Office of Communications በስልክ ቁጥር፡- 240-740-2837፣ 1-800-735-2258 (Maryland Relay) ወይም PIO@mcpsmd.org በመጠየቅ ማግኘት ይቻላል። የምልክት ቋንቋ ትርጉም የሚያስፈልጋቸው ግለሰቦች የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ የትርጉም አገልግሎት ጽ/ቤትን በዚህ ኤሜይል ወይም በስልክ መጠየቅ ይችላሉ። MCPS Office of Interpreting Services ስልክ ቁጥር 240-740-1800, 301-637-2958 (VP) mcpsinterpretingservices@mcpsmd.org, ዐወይም MCPSInterpretingServices@mcpsmd.org

ሀምሌ 2024